

# ለመምህሩ!!
# ለአባ ኮስተር የኔሰው ገብሬ

”ወጣቶች ተምረን- ሆነን መልካም ዜጋ
ማየቱ ብቻ ነው - የመምሕራን ዋጋ
የመምሕራን ሁሉ - ሐዋርያው ይጽና
ለዘላለም ይኑር - ጥበብ እንዳበራ ...”
ብሎ አዘምሮ ዕውቀት - አሽምቶ
ከድቅድቅ ጨለማ-ወደ ብርሃን መርቶ
መንገድ አሳይቶ - ሕይወቱን ሰውቶ
እንደሻማ በርቶ - ሁሌም እየቀለጠ
ድካሙ ልፋቱ - ከሁሉ የበለጠ
ታላቁ መምሕር- የኔ ሊቃውንት
ለሕልፈተ ሕይወት በቃ- ከፈለ ሕይወት::
መንገዱ ጠፍቶብን - ሊያሳየን ጎዳና
በቀን ጨልሞብን - መሪ አጣንና
መምሕሩ ተነስቶ - አትፍሩ አለና
ለነጻነትህ ሙት - ፍርዱ እንዲቀና
ፍርሃትን አስወግድ - ታገል ተነሳና
ብሎ መንገድ ሊያሳይ - የነጻነት ፋና
የሁላችን የኔሰው- የብዕር አባት
ትላንት ተሰዋልን -ወሰደው አሉ ሞት
አንቺ የኔሰው እናት - ጀግና የወለድሽ
ምንኛ የታደልሽ- ታላቅ እናት ነሽ
አደራ ብዬ አለሁ- ሙሾ እንዳትወርጂ
እንባ እንዳታነቢ - መልሰሽ ውለጂ
ደጋግመሽ ውለጂ !!


መይሳው ከምድረ
ስዊድን


EthioLion.Com